እንኳን አደረሳችሁ

በዓሉን የአማን ያድርግላችሁ።

የትንሣኤ በዓል ልዩ ዕትም

ቅዳሜ ሚያዝያ 21/2013 ዓ.ም

በየሁለት ሳምንቱ ለህትመት የሚበቃ

ልጅነት እና የፋሲካ ትውስታ

ኤልሳ ሙሉጌታ - ደራሲና ተርጓሚ

የጋሻው አዳልን ማለዳ የሚል ዘፈን እያቋጨ፣ የሬክታንግል ቅርፅ ካለው የእንጨት ፍሬም ላይ አቡጀዲውን ወጥሮ ግድግዳ ላይ አስደግፎት፣ እርሱ በርጩማ ላይ ተቀምጦ እግሩ ስር ከተቀመጡ ትናንሽ የቀለም ጣሳዎች ብሩሹን እየጠቀሰ፣ አቡጀዲው ላይ በእርሳስ የነደፈውን በቀለም ሲያደምቅ አጠገቡ ነበርኩ።

መሳል ይወዳል አባቴ። ቴሌቪዥን ባልነበረበት ትንሽ የገጠር መንደር ውስጥ የትምህርት ቤታችን ክፍሎች ግድግዳ ላይ እነ አክሱም ሃውልትን፣ እነ ላሊበላ መቅደስን፣ እነ ዋልያን እየሳለ ለብዙ አኩዮቼ ያስተዋወቃቸው እሱ ነው። ስዕሎቹ ስር የሚፃፉት የእሱ እና የአባቱ ስም መጀመሪያ ሁለት ፊደላት ደግሞ ከእርግጫ እና ከሁካታ አረፍ ብለው ስዕሉን ከሚቃኙ ስለ አክሱም ቁመና ስለ ዋልያ ቀንድ ስለ ላሊበላ ቅርፅ ከሚጨቃጨቁ ህፃናት በተለየ ለኔ ትልቅ ትርጉም ነበረው።

እነሱ ስዕሎቹ ላይ ሲጨቃጨቁ እኔ በአይኖቼ የምፈልገው፣ እጄን ልኬ የምዳብሰው፣ ከስዕሉ ግርጌ የሚኖረውን የአባቴን እና የአያቴን ስም የመጀመሪያ ፊደላት ነው።

ያም የኩራቴ ምንጭ ነበር።

አባቴ አቡጀዲ ላይ መሳል የጀመረውን፣ ከንድፉ ጀምሮ የማውቀውን ያንን ስዕል ከቀናት በኋላ አጠናቆ ለሃሳቡ መሙላት የተሳለው ተሳክቶለት፣ እጅ መንሻውን ለክብሯ ለምልጃና በረከቷ፣ በራሱ እጅ የሳለውን ምስል ለክርስቶስ ሳምራ ቤተክርስቲያን ያስገባ ቀን እጅግ ከፋኝ ።

አለ አይደል የለመዱት ሲሄድ ቅር እንደሚል ነገር ልክ እንደዛ ...

ከጥቂት ጊዚ በኋላ - ለህማማቱ ቁር ባረበበት ጉም ደርቦ በተኛ ብርዳም ማለዳ፣ እግዜር የፍጡራኑን ፀሎት ሊሰማ የሰማይ መስኮቶችን ሁሉ ከፍቶ ለተፈጣሪው ጆሮውን በሚያውስበት ንጋት 11:00 ሰዓት ከአጥቢያችን ክርስቶስ ሰምራ ቤተክርስቲያን የሚመጣ በስርቅርቅ ድምፅ የተዋበ ፀሎተ ምህላ ከጥልቅ እንቅልፌ እንደ አይን ጥቅሻ የሚያነቃኝ ልብ ቆርቋሪው ዜማ ተነስተሽ ሂጂ ሂጂ እያለኝ፤ እየተጨናበስኩ ከመኝታዬ ነቅቼ በሰሞነ ህማማቱ መሬት በጫማ አልረግጥም የምል፣ የጌታን ህማም መከራ በባዶ እግሮቼ ልጋራ የማልደነግጥ፣ ለእንቅፋት የማልበረግግ ለእሾህ፤ የቤታችንን በር ከፍቼ ሊፈግግ ያለን ጨለማ በድፍረት የምቀላቀል፤ ተስፋ እምነት ፍቅር ተባብረው የሚያጁቡኝ ብላቴና ነበርሁ።

ከበስተኋላዬም የእናቴ ድምፅ ተከትሎኝ << ኧረ ወገግ ይበልልሽ ልጄ ጅብ ይለቃቅምሻል >> እያለችኝ።

ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፤ እለተ አርብ ስቅለቱ ቤተ ክርስቲያን ደርሼ የበራፏን መቃን ስሜ የቅድስቷን መጋረጃ በሃምራዊና ቀይ ያማረ ከርቤው የሚያውደውን እጄን ሰድጄ ዳብሼ በረከቱ እና ግርማው ልቤን እየሞላኝ ሰርክ እለት ከማስቀድስበት ከምቆምበት ስፍራ ስገኝ በኪራላይሶ መሃል ስቃና ከተንበረከኩበት ከፋት ለፋቴ ግድግዳ ላይ ምስሉን ተሰቅሎ አየሁት ::

አባቴ አቡጀዴ ጨርቅ ወጥሮ እርሳሱን ቀርፆ ገና ሊስለው ሲነድፍ ያኔ ጀምሮ የማውቀው፣ ምስለ እየሱስን አየሁት :: የእያንዳንዷን ቀለም ጣሳ፣ የተቀባበትን ቡሩሽ፣ የቀቡትን የአባቴ እጆች ሁሉን ጠንቅቄ የማውቅለት ምስለ እየሱስን ከፊቴ ከግድግዳ ላይ አየሁት።

በፀጥታ ተጠግቼ ፊት ለፊቱ ቆምኩኝ፤ ከግራ እጁ በላይ በኩል ጲላጦስ በሶስት ቋንቋ የፃፈው ደብዳቤ ከመስቀሉ ጋር ካያያዘው 'ሮዳስ' ከተባለው ችንካር ተነስቼ የግራ እጁ መዳፍ መሃል ያለውን 'ዳናት' ነክቼ ወደ ቀኝ እጁ ሳቀና 'አላዶር' ቀኖት (ሚስማሩ) ግራው ላይ ካለው የበለጠ መሰለኝ፤ ጥቁር አናት ባለው ችንካር በተነደለው መዳፉ መሃል የደም ነጠብጣብ እየወረደ ....።

በቁስሉ እንደፈወሰኝ ህማሙ ልቤን ተሰምቷት ስቃዩ ነፍሴን ሰርስሮኝ፤ እርሱን እንደሰቀሉት ሁሉ ምስሉን በሳለው አባቴ አቂሜ ተበሳጭቼ << አባዬ ለምን ጨከነበት እንዲህ >> እያልኩኝ።

እጆቼን አንሸራትቼ ወገቡ ላይ ያለች እራፊ ጨርቅ ተደራርበው የተቸነከሩ እግሮቹን አያለሁ፤ ባለ መጎናፀፊያውን እርሱን በብጣሽ ጨርቅ ያስቀረ፤ ለእግሮቹ መረገጫ ምድር የምትጠበው እርሱን ወርዱ ክንድ ባልሞላ እንጨት እግሮቹን ያነባበረ፤ ለቃሉ ሰማይና ምድር የሚያልፋለት እርሱን ያስዘባበተበት፤ ይህ ሁሉ ለምን በእርሱ ሆነ ብል -'ምክንያቱ ፍቅር ነው' አሉኝ ::

ይህን ህመሙን አይቼ ከምስሉ ግርጌ ሳማትር የልጅነቴ ቀናቶች የኩራቴ ምንጭ መሰረት እኒያን ሁለት የአባቴን ስም መጀመሪያ የሆኑ ፊደላት አየሁ ይሄኔ ጎኔ ወደነበረችው ጓደኛዬ ጆሮ አፈን አሹዬ << አየሽው ምስሉ ላይ ያለውን ሰው?... ከሁላችሁም የበለጠ እኔን በደንብ ያውቀኛል >> አልኳት።

<< የቱ ? ይሄ ?>> አለችኝ ስዕሉን ከሌሎች ስዕሎች ነጥላ እያመለከተችኝ ::

እጆቿን ተከትዬ የደም አበላ ከሚወርድበት ቁንዳላው የሾህ አክሊል ከደፋበት ራሱ በላይ ተፅፎ መስቀሉ ላይ የተቸነከረውን ምስኪን ሰው እያየሁ ::

ረገጥ አድርጌ ደረቴን ነፍቼ መለስኩላት << አዎ ...ይህ ሰው ከሁላችሁም የበለጠ የሚቀርበኝ ለእኔ ነው >>

ሰሞነኛ

© ምስል - በህሊና ታፈሠ

ከሥራ ቦታ ወደ ሰፈር (ለቡ) ስንሄድ መንገድ እየተዘጋጋ አንዳንዴ ለስሁር የምንደርሰው ነገር (ግነት) ፣ ቴምርና ውኃ መያዝ ልምድ አድርገን እንደኛው መንገድ ላይ አዛን ካለባቸው ጋር በመስኮት የምናፈጥረው፣ አልፎ አልፎ ሰብሰብ ብለን ውጪ እናፈጥርባቸው የነበሩ ዓረቢያን ሬስቶራንቶች ሸር ጉድ፣ በየመንገዱ ላይ ያሉት፣ በሙስሊም ሰልፈኛ የሚጨናነቁትና መዓዛቸው የሚያውደው ዘመናዊ ዳቦ ቤቶች፣ በተለይ የምወደው የነበረው የቴምር ዳቦ፣ በብኹርና ነሸዳዎች የሚታጀቡ የንግድ ድርጅቶች፣ ከመብራት ሃይል ጀምሮ እስከ አባድር ከዛም እስከ እኛ ሰፈር ድረስ የሚኮለኮሉት በዬአመቱ የሚመጡ ነዳያን (በብዛት ተፈናቃዮች)፣ ጀለቢያ ለብሰው፣ ሙስባሃቸውን አንግበው፣ ኪታብ ሸጎጥ አድርገውና ደረሳ ቢጤ አስከትለው የሙስሊም ቤት እየጠየቁ የሚመጡ አራዳ "ገሪባዎች" ራሳቸውን የቻሉ ድምቀቶች ነበሩ።

የመርካቶ አንዋር መስጅድ ዙሪያን ከወትሮው የተለዬ የገበያ ግርግር፣ ቴምሩን፣ እጣኑን፣ የምንጣፍ የመጋረጃ ገበያውን፣ የሸይኽ ጦሃን "ዓለይከ ረበና" ያማረ ድባብ ካለው ተራዊሕ ጋር፣ ሁሉን እንደ አቅሙ የሚያስተናግዱትን የሾርባና የሳምቡሳ ጉሊቶች ማን ይረሳል?! ባልደርስባቸውም እነ ሐጂ ዙልመካ፣ እነ ሐጂ ዘይኑና ሌሎች ትላልቆች በርካታ ረመዷንን ባሳለፉበት ባለ ሀይባ ከተማ መገኘት ደስ አይልም?

የተራዊሕን ሶላት ብዙ ሰዎች እየተዘዋወሩ በተለያዩ መስጅዶች የመስገድ ልምድ አላቸው። እኔ ሰፈሬ ራቅ በማለቱ የታላላቆቹ ኑርና አንዋር መስጅዶችን ድባብ ለማዬት አልያም በተለዬ አጋጣሚ ካልሆነ በስተቀር ከበኒን ቀጥሎ የኔ ተወዳጅ መስጅድና የተራዊሕ ደንበኛ ደመቅ ባለው ላፍቶ ሰፈር የሚገኘው የተንጣለለው ቢላል ነበር። ንቁውና ቀልጣፋው ኢማም ሸይኽ ሙሐመድ ጦይብ ቀደም ብለው በማራኪ አንደበታቸው ዳዕዋ ይጀምራሉ። የዒሻ ሶላት ከተጠናቀቀ በኋላ የተራዊሕ ሶላቱን ማስጀመሪያው የሙዓዚኑ "አሽሀዱ አንላኢላሃ ኢለሏህ አስተግፊሩላህ፣ ነስአሉከል ጀነተ ወነዑዙቢከ ሚነናር አሏሁመ ኢነከ ዓፉውን ቱሂቡል ዓፍወ ፈዕፉአና ቢረህመቲከ ያአርሃመራሂሚን" የሚለው አሳዛኝ ድምፅና ሰጋጁ በዜማ ተከትሎ የሚለው ነገር አይረሳኝም። "አስሶላተል ጃሚዐ ሶላተ ተራዊሕ" የሚሉትንም አሁን የምሰማው ነው የሚመስለኝ። በየመሃሉ ያለው ዱዓና አዝካር ከውስጤ አይጠፋም። ተራዊሑ በ "ዓለይከ ረበና" ተቋጭቶ ለዊትር ከመቆማችን በፊትም "ነወይቱ ሰውመ ኻዲን አን አዳዒ ሸህሪ ረመዷን ሀዚሂ ሠነቲ ኢማነን ወህቲሳበን ሊላሂ ተአላ" የሚሉትን እያሰብኩ አሁንም እነይታለሁ።

መካኒሳ ቆሬ አካባቢ የአደሬዎች መስጅድ አለ። ዚክሮቻቸውም እነሱም ደስ ይሉኛል። ዲኑን ለትውልድ ያስተላለፉበት ቀለል ያለ ውብ መንገድ ይማርከኛል። ሌላው ሱዳን ክለብ ነው። የሱዳኒው ኢማም ቁርዓን አቀራር፣ የሰፈሩ ድምቀት፣ የመኪናው ትርምስ፣ የሰው ነሻጣ፣ ያወቀ የሚያውቀው የJuice ክትባትና የወራቄ ግሪን ፎረስት ወረፋ አይረሱም። አንስቼ የማልጨርሰው ሆኖብኝ በቅርበት የማውቀውን ብቻ አነሳሁ እንጂ ሸገር ከአብነት እስከ ኳስ ሜዳ፣ ከአውቶብስ ተራ እስከ መሳለሚያ፣ ከመርካቶ እስከ ላፍቶ ረመዷንን የሚያስናፍቁ የሰፈር ትዝታዎች ባሏቸው አካባቢዎች ነው የተሞላችው።

እንደ ሌሎች ቦታዎች ሁሉም ሸገርም በረመዷን በቸርነትና ደግነት አየር ትከበባለች፤ በአብሮነት ትደምቃለች። ቤታቸው ምግብ ሰርተው ለሚስኪን የሚልኩ፣ በዓይነትና በገንዘብ የሚደግፉ፣ ካላቸውም ላይ ሆነ ያላቸውን የሚሰጡ፣ ገንዘብ ቢጎድላቸው ግና ፍቅር ተርፏቸው ያገኟትንም ተካፍለው የሚበሉ እልፍ ናቸው። ዛሬም በዚህ የችግር ወቅት ይህ ልምድ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ባሰብኩ ጊዜ ደስስ ይለኛል!

ረመዷን ሙባረክ!

ህይወትህን በጥበብ ምራት

ጌቱ ከበደ ኪዳኔ
የኢንጂነሪንግ፣ የምግብ ቴክኖሎጂ እና የማኔጅመንት ባለሙያ፤
የቢከን (መሪ መብራት) መጽሐፍ ደራሲ።

ህይወትን በጥበብ መምራት ለሁሉ የተገለጠ አይደለም። ጤናህን፣ ሰላምህን፣ ቤተሰብህን፣ ገንዘብህን፣ ግንኙነትህን አስደሳችና አስተማማኝ ማድረግ ሁሉም የታደለው አይደለም። በጥበብ የሚኖሩት ግን ይህ ይቻላቸዋል።

ብዙ ገንዘብ፣ ብዙ ሩጫና ጂም፣ ብዙ ትምህርት፣ ብዙ ጓደኛ ሳይሆን ትንሽ ጥበብ ህይወትህን አስደሳች ታደርገዋለች።

ብዙ ዲግሪ ይዘው እውቀት የሌላቸው አሉ። ጠዋት ማታ ስፖርት እየሠሩ ጤናማ ያልሆኑ አሉ። ፋብሪካና ሀብት ኖሯቸው ሰላም እና እንቅልፍ ያጡ አሉ። ድካምህ በጥበብ ካልሆነ ትርፍህ ድካምና ስም ብቻ ይሆናል።

ድመቷን እያት! ጽዱ ነች። ጥሩ ትተኛለች፣ ተኝታ ስትነሳ ትንጠራራለች stretch ታደርጋለች። ሥራ ሲያጋጥማት ሥራዋን በትኩረት ታከናውናለች። ጫጫታና ጩኸት የላትም። ሲላት የአሳዳሪዋ ጭን ላይ እንደ ላፕቶፕ ትቀመጣለች። የተፈጥሮ ግዴታ የሆነውን ቆሻሻዋን ማንም እንዳያየው አድርጋ ትቀብራለች ወይ ትሸፍናለች። ነውሯን ትደብቃለች። ስታረግዝ እንጂ ስትዳራ እንኳ አታያትም። [አንዳንዶች ከድመት አንሰው መዳራትን በአደባባይ እያሳዩን ነው።] ከድመት ብዙ መማር እንችላለን። እንደድመት ሁሉ ከሌሎች እንስሳትም የምንማረው በጎ ነገር አይጠፋም።

ዛሬ ምን አቅደሃል? ሳምንቱ እንዴት ያልፋል? እንዳለፈው?

ከተመቸህ መልካም! ካልተመቸህ ግን ለውጥ ያስፈልግሃል። በማለዳ ወፍ ሳይንጫጫ ተነስ! አምላክህን በጤና ስላሳደረህ አመስግን፣ ቀንህን እንዲባርክልህ ጠይቅ። ተንጠራራ! ነቅነቅ፣ ወዝወዝ በል፣ ፑሻፕ ሥራ፣ ገመድ ዝለል። አትክልቶችህን ውኃ አጠጣ። እንስሳቶችህን መግብ፣ ተጣጠብና ለባብሰህ ለሥራ ተዘጋጅ። እቅዶችህን ተመልከትና መስተካከል ካለባቸው አስተካክል። ለእቅዶችህ ስኬትና ለውሎህ መልካምነት ፀልይ!

ዜናዎችን ገረፍ ገረፍ አድርግ። አስፈላጊ ለሆኑ መልእክቶች መልስ ስጥ። አስፈላጊ የንባብ ዝግጅቶችን አድርግ። አንብብ! ተነቃቃ፣ ሌሎችንም አንቃ! ፀሓይዋ ስትወጣ ተመልከት። ቀርስህን መጥነህ ቅመስ ተቃመስ ብላ!

በጊዜ ወደ ሥራህ ሂድ! በመንገድ ላይ ዜና ስማ። ጠቃሚ ነገር አንብብ። መጽሓፍት ሲነበቡ ስማ። ሥራህን በእቅድና በደስታ መንፈስ ጀምር። በርትተህ ሥራ! ስብሰባ አታብዛ። ቢያንስ በየሰዓቱ እረፍት አድርግ፣ ተንጠራራ ቁጭ ብድግ በል። በየእረፍት ሰዓት ለሌሎች ደውል፣ መልእክት ጻፍ። ሌሎችን ጎብኝ። ሥራህን በየ2 ሰዓቱ ገምግም። ሥራህን ስትጨርስ አጭር ማስታወሻ ጻፍ። ምሳህን ከወዳጆች ጋር መጥነህ ብላ፣ ተጫወት።

ማታ ወደቤት ስትመለስ ተጣጠብ። ውሎህን በአጭሩ ከትብ። እራትህን በጊዜ ከመረጥከው ሰው፣ ጓደኛ ወይም ቤተሰብ ጋር በልክ ብላ። ከእራት በኋላ ከቤተሰብ ጋር ወይም ከጓደኛ ጋር አጭር የእግር ጉዞ ሽርሽር አድርግ፣ ተጫወት። በጊዜ ክፍልህ ግባና ዜና ተመልከት። የቀኑን ውሎ ገምግም። የህይወትህን ጉዞ ገምግም። የነገን ውሎ፣ የሳምንቱን ሥራ፣ የህይወትህን ጉዞ አቅድ። ፈጣሪህን አመስግን፣ ፀልይ። በጊዜ ተኛ።

ለሁላችንም ስኬታማ የሚያዝያን ወር ተመኘሁ።
መልካም የትንሣኤ በዓል!

እንትያ ሰላንቲያ

ነገረ-ሕግጋት

በካፒታል ክብረ - የህግ ባለሞያ እና በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የህግ አማካሪ

1. በ**1952** ዓ.ም. በወጣውና አሁንም በስራ ላይ ባለው ፍትሃብሄር ህግ አንቀጽ **2115** መሰረት ባል ሚስቱ ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሳ መጠየቅ ይችላል። በዚህ አንቀጽ መሰረት ባል ሚስቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ እና በደረሰባት ጉዳት ምክንያት፣

- ለባሏ የምትሰጠው ጥቅም እና
- ለባሏ የምትሰጠው ደስታ ከቀነሰ ባል የህሊና ጉዳት ደርሶብኛል እና የህሊና **(**የሞራል**)** ካሳ ይከፈለኝ የሚል ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል።

ሆኖም ሚስት ለባሏ የምትሰጠው ደስታ እና ጥቅም ምን እንደሆነ ህጉ አላብራራም። እንዲሁም በደስታ እና በጥቅም መካከል ያለው ልዩነት በተገቢው አልተብራራም።

በተጨማሪም ይህ የህግ ክፍል ባል ላይ ለሚደርስ ጉዳት ለሚስት የህሊና **(**የሞራል**)** ካሳ የመጠየቅ መብት አልሰጠም።

2. በ**1952** ዓ.ም. በወጣውና አሁንም በስራ ላይ ባለው ፍትሃብሄር ህግ አንቀጽ **2116(**ሐ**)** እንደተመለከተው የህሊና **(**የሞራል**)** ጉዳት ካሳ ከአንድ ሺ ብር ሊበልጥ እንደማይችል ተደንግጓል።

ስለሆነም በአሁን ወቅት የህሊና ጉዳት ደርሶብኛል የሚል አካል ከአንድ ሺ ብር በላይ መጠየቅ አይችልም። ሆኖም ይህ ህግ በወጣበት ወቅት አንድ ሺ ብር ከነበረው ዋጋ አንጻር እና አሁን አንድ ሺ ብር ካለው ዋጋ አንጻር ህጉ ሳይሻሻል አሁንም ተፈጻሚ መሆኑ አስገራሚ ነው።

3. በ**1952** ዓ.ም. በወጣውና አሁንም በስራ ላይ ባለው ፍትሃብሄር ህግ አንቀጽ **30** መሰረት እያንዳንዱ ሰው አንድ የቤተ ዘመድ ስም አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞች እና የአባት ስም እንደሚኖረው ተደንግጓል። ሆኖም ይህ የስም ስርአት ተግባራዊ ማድረግ ባለመቻሉ ምክንያት በተለምዶው የቤተሰብ ስም የሚባል የለም። በልምድ የሚታወቀው የግል ስም ፣ የአባት ስም እና የአያት ስም መሆኑ ይታወቃል።

ስለሆነም በሃገሪቱ የስም ህግ መሰረት እያንዳንዱ ሰው የቤተሰብ ስም ሊኖረው እንደሚገባ እንደመደንገጉ መጠን በአሁን ወቅት ጥቅም ላይ ያለው የስም ስርአት ህግን ያልተከተለ እና የሃገሪቱ ሙሉ ህዝብ ህጋዊ ስም የለውም የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርሰን ይሆናል።

ጠሊቅ

ቴዎድሮስ ገብሬ
አዲስ አበባ ዮኒቨርሲቲ
በቋንቋ እና ባህል ዲፓርትመንት ረዳት ፕሮፌሰር

“ተፈጥሮ ሃይማኖትና ታሪክ የኢትዮጵያ ሮማንስ የተመሰረተባቸው አእማድ ይመስሉኛል። የኢትዮጵ ምድር የማይታረቁ የሚመስሉ ተፈጥሮአዊ ገጽታዎች፣ ለምሳሌ የራስ ዳሸንን ከፍታ ከዳሎል ጥልቀት ጋር አዛንቆና አስማምቶ የያዘ ነው “የአሥራ ሦስት ወር የፀሐይ ብርሃን”፣ “የአፍሪካ የውሃ ማማ፣ የመካከለኛው ምሥራቅ የእህል ጎተራ”፣ “የሰው ልጆች መገኛ” (በሳይንሱም በሃይማኖቱም ጠገግ)፣ ወዘተ የሚሉት ስያሜዎች ነባር የኢትዮጵያ መለያ ምልክት (popular imagery) አካል ናቸው።

ሁለተኛው የሮማንስ መመሥረቻ አምድ ታሪክ ነው። “ኢትዮጵያ” የሚለው ቃል ሦስት ሺህ ዘመን ያስቆጠረ ያለው ባህል፣ ሱዳን፣ ጂቡቲ፣ ግብጽ፣ የመንና ሳውዲ አረቢያ ድረስ የተዘረጋ ኃያል ክንድ የነበረው ሕዝብ፤ ከአራቱ ታላላቅ ጥንታዊ ኢምፓየሮች መኃል- ከፋርስ፣ ከቻይናና ከሮማ ጋር አንዱ የነበረ ግዛት መጠሪያ ነው።

በሃይማኖቱም ረገድ ኢትዮጵያ ማክስ ዌበር “world religions” የሚላቸው ሁለቱ ሃይማኖቶች፣ ክርስትናና እስልምና ቀድመው የተሰበኩባት፣ እስራኤላውያን ከአምላክ ጋር ላወረዱት እርቅና ለፈጸሙት ቃል ኪዳን ቋሚ ምስክር የሆነው የሙሴ ጽላት የሚኖርባት፣ የመጀመሪያዎቹ ሙስሊም ስደተኞች የተጠጉባት፣ በዚህም የነቢዩ መሐመድ ዘላለማዊ ምህላ (eternal immunity) የወረደላት አገር ናት።

ይህ ከቅድመ ዓለም እስከ ድኅረ ዓለም የተዘረጋ ራስ ምስላ (self portrait) ለረጅም ዘመን በሃይማኖቱ፣ በታሪኩ፣ በፖለቲካው፣ በኪነቱ ገንኖ የኖረ ሮማንስ ነው።”

ምንጭ - (መልክአ ስብሃት ገጽ 56-57)

ዝክረ - ደራሲያን

ከበደ ሚካኤል

ከበደ ሚካኤል (1909-1991) በደብረ ብርሃን ከተማ ኣካባቢ፣ ገርም ገብርኤል አጥቢያ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፱ ዓ.ም.ተወለዱ። ወደ አዲስ አበባ እንደ መጡ መጀመሪያ በአሊያንስ ኢቲዮ-ፍራንሴዝ በኋላም በላዛሪስት ሚሲዮን ትምህርታቸውን ተከታተሉ። የሼክስፒርን ሮሜዎና ዡልየትን ማክቤዝን በመተርጎም እውቅናን ለማትረፍ ችለዋል።

ከሰሯቸው ታዋቂ የትርጉም ሰራዎች መሃል፣ 'ከይቅርታ በላይ' በሚል አርእስት ከ Beyond the Pardon በ M.Clay የተተረጎመው የሚጠቀስ ነው።

ከበደ ሚካኤል 30 ገደማ መፃሕፍትን ፅፈዋል። ከበደ ሚካእል ካበረከቷቸው የቴአትር ስራዎች መሃከል፦

የትንቢት ቀጠሮ
የቅጣት ማእበል
ካሌብ
ሃኒባል

ይገኙባቸዋል።

ከበደ ሚካኤል በርካታ የስነ ጽሁፍ ስራዎች ባለቤት በመሆናቸው በተለይም ለልጆች ትምህርት አዘል ጽሁፎችን፣ የግጥም የፈጠራ ስራዎችን፣ ቅኔዎችን በስፋት በማበርከታቸው በኢትዮጵያ የስነጽሁፍ መድረክ ገናና ከሆኑት ደራሲዎች ውስጥ አንዱ ናቸው። ከነዚህም መሃል፦

ታሪክና ምሳሌ ፩
ታሪክና ምሳሌ ፪
የህሊና ብርሃን
የቅኔ ውበት
ጃፓን እንዴት ስለጠነች
ታላላቅ ሰዎች
የሥልጣኔ አየር ሊጠቀሱ ይችላሉ።

የሰዎች ስነ ምግባር ላይ የማተኮርና ምክር አዘል መልእክቶችን የማስተላለፍ ዝንባሌአቸው በአብዛኛው ስራቸው ላይ ይንጸባረቃል።

ዘመናዊት ኢትዮጵያን ለማደርጀት በተደረገው ትግል በግንባር ቀደምትነት የተሳተፉ እኒህ ፈላስፋ፥ ባለቅኔ፥ ጸሐፌ-ተውኔት፥ ደራሲና አንጋፋ ጋዜጠኛ ፥ 'የቀለም ሰው' በሀገራችን የመጀመሪያ የነበረውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት በቀዳሚነት የተቀበሉ ሲሆን፣ አዲስ ትውልድ ላፈራ ስብእናቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፯ ዓ.ም. በሥነ ጽሑፍ የክብር ዶክቶሬት ዲግሪ ሸልሟቸዋል። በተረፈም ከፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ሶቭየትህብረትና ሜክሲኮ ሽልማትን ተቀብለዋል።

በተረፈ የትምህርት ሚኒስትር ዳይረክተር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተከታይ ዳይሬክተር (፲፱፵፪)፣ የብሄራዊ መጻህፍት ቤት ዳይረክተር (፲፱፵፩)ና የካቢኔ ሚንስትር ሆነው አገልግለዋል።

ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል፥ ኢትዮጵያዊ 'የቀለም ሰው' ኅዳር ፫ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. በሰማንያ ሁለት ዓመታቸው አረፉ።

ሀገር አማን ይሄንን አጠር ያለች የከበደ ሚካኤልን ግጥም ትጋብዛለች።

የተማረ ሆኖ እውነቱን የማይገልጽ ፣
ባለ ጸጋ ሆኖ ገንዘቡን የማይሰጥ፣
ደሃ ሆኖ መስራት የማይሻ ልቡ፣
ሶስቱም ፍሬ ቢሶች፣
ለምንም አይረቡ።

(ይገርመኛል እንጂ!)

አዱኛ ሌሊሳ፣ ከቨርጂንያ፣ አሜሪካ

ኮስማና ገላዬን ብርዱ እየገረፈው፣
የማለዳ ጤዛ እግሬን እየላፈው፣
"ከንዱ" ሲል ከንድቼ --ሰርክ የምሰለፈው፤
ቁር 'ሚያናፍጠው- እልፍ አእላፍ ማቲ -ጎኔ ተደርድሮ ፣
"ኢትዮጲያችን ኑሪ" -እያለ ሲዘምር- እጆቹን ወድሮ ፣
ኧሮ...
ይገርመኛል እንጂ!!
-
እቺ "ኢትዮጲያ" 'ሚሏት -ወለሎቹ ሁሉ -ጮኸው የሚጠሯት፣
ይሄ ሁላ ልብ ውስጥ -ማን ምሶ ቀበራት?
ምን ታምር ወለዳት?? እንደምን ያለሰው??
መንፈሷ እያሳሳ ስሜት የሚያርሰው?

(በጨዋታ መሃል)

ስሟን እያነሳ መምሩ 'ሚያለቅሰው??
መች ፍቅሯን ቀመሰው??
መች ደላው እንደሰው??..መች ተኝቶ አድረ??
ኑሮ እየደቆሰው እየተቸገረ??
"ሃገራችን" የሚል ..እንባ እያቀረረ???
ኧረ...
ይገርመኛል እንጂ...
-
ምን አይነት ፍቅር ነው?? እንዴት ያለ ተምኔት??
ተገፍተው -- ተረግጠው --ወድቀው በሰው መሬት
በእንባ እየታጠቡ--- "ኢትዮጲያዬ" ማለት...



የንባብ ልምድና ፍቅር እንዴት ይመጣል?

ከአሳፍ ሃይሉ - ከአሜሪካ

ብዙዎች የንባብ ልምዴን እንዳካፍል ይጠይቁኛል። ሌላ የተለየ ተዓምር የለውም። እንደ አትክልት ነው የሚመጣው። እንደ ዶሮ። እንደ በግ። እንደ ህጻናት አስተዳደግ ነው የሚመጣው። ንባብ ዝም ብሎ አይመጣም። ከልጅነት የምታዳብረው ልማድ ነው። አንድን የጥድ ዛፍ ከሆነ ቦታ ከነነፍሱ ነቅለህ እቤትህ አትተክለውም። ትንሿን ችግኝ ነው የምትተክላት። የማንጎ ፍሬዋን በስታ የወጣችውን ትንሽዬ ሥር ነው አምጥተህ የምትተክላት። ትንሽዬው ድክ ድክ የሚል ቡችላ ነው ታማኝ የቤተሰብህ አለኝታ ሆኖ የሚያድገው - ውሻ ከሆነ። በግም ከሆነ። ዶሮው የሚረባልህ እንቁላሉን በትዕግሥት አስታቅፈህ አስፈልፍለህ ነው። ጫጩቶቹን ተንከባክበህ አሳድገህ ነው።

«The Curious Case of Benjamin Burton» በሚለው ፊልም ላይ ሽማግሌ ሆኖ እንደሚወለደው ታዋቂ ተዋናይ ብራድ ፒት - ህጻናት ሁሉ በአንዴ ሸምግለው አይወለዱም። ከፅንሰት እስከ ውልደት፣ ከወተት እስከ አጥንት፣ ከመዳኽ እስከ ድክ ድክ፣ ከድክ ድክ እስከ ህይወት ሩጫ፣ ወጣትነትና አንጋፋነት፣ ብሎም ሽምግልናና ምዉትነት በአንዴ ዘው ብለው አይገቡም። የዚህ ዓለም ነገሮች ሁሉ ከትንሿ ጥቂት ነገር ወደ ትልቁ ግዙፍ ነገር ጥቂት በጥቂት እያሉ የሚመነደጉ ክስተቶች ናቸው።

ንባብም እንደኔ አረዳድ ከዚህ የተፈጥሮ ህግ ውጪ አይደለም። በልጅነት ድክ ድክ የሚጀመር የማወቅ ፍቅር ነው። ቀስ በቀስ እንደ ኳስ ጨዋታ በቀሽም ስልት የሚጀመር የተሸሞነሞነ ጥበብ ነው። እንደ ቴኒስ ጨዋታ ራኬትህን እያወላገድክ፣ እየፎረሽክ፣ መከራህን እየበላህ የምትጀምረው - አንዴ ጨዋታውን ስታውቅበት ደግሞ በፍቅር የምትወድቅለት፣ ቀስ በቀስ ሱስ የሚሆንብህ - የህይወት ዘመን ልማድ ነው ንባብ።

አንድን የጎለመሰ ሰው አምጥተህ በስተርጅና ኳስ ጨዋታን አታስተምረውም። ሌላንም ጨዋታ። በአንዴ የሚመጣ አይደለማ። ከልጅነት የዳበረ ልማድ ውጤት ነውና። በእርግጥ ከዘገየ ጥቅሙንና ደስታውን አውቀው ጀምረውት የተዋጣለቸው አንባቢ የሆኑ ሰዎች ይገኙ ይሆናል። የራሴን የንባብ ልምድ ጅማሮም ሆነ የብዙ ሰዎችን ምስክርነት ተመርኩዤ እኔም ስለ ማንበብ ልምድ የምናገረው እውነት - የማንበብ ልምድ ከህጻንነት ተውተርትረህ የምትጀምራት የዕድሜ ልክ ሱስ ነች የሚል ነው። ከህጻንነት በትንንሿ የተረት መጻሕፍት ይጀምራል የማንበብ ልማድ። የእኔ ዘመን ልጆች - የዘመን እኩዮቼ ኢትዮጵያውያን የማንበብ ልማድም በትምህርት ቤት የሚሰጡ የመማሪያ መጻሕፍትንና የመማሪያ ደብተሮችን ከማንበብ ብቻ ሳይሆን - እነዚያን ትናንሽዬ ገጽ ያላቸው - ግን ጣፋጭ ምናብን ከሚስሉልን ትናንሽዬ መጻሕፍት በማንበብ የተጀመረ ልማድ ነው።

ከልጅነቴ የንባብ ፍቅርን በውስጤ ከዘሩብኝና ከማስታውሳቸው ጥቂት ተረት-መሣይ የህጻናት መጻሕፍት ኳስ ተጫዋቹን ህጻንና የሰፈሩን ልጆች የሚተርከው «የግችሌ ሜዳ»። ትልቅ ጫማ ሰፍቶ ጉድ ያስባለው ትንሹ «ዶጮ»። ሀገሩን ሁሉ በጣፋጭ ገንፎ የሞላው ህጻን «የገንፎው ተራራ»። ከሩሲያ የህጻናት ተረቶች የተተረጎሙት «ቲሙርና ቡድኑ»። «ነጩ ቁርዬ በሚኖርበት»። እንደ ፒኖኪዮ ከእንጨት ገጣጥመው ሳይንቲስት አባቱ የሰሩትና ተዓምረኛ የሆነው ህጻን «ቴሪዎሼችካ»።

እንዲያውም የዚህን ተረት መዝሙሮች በልጅነታቸው ከሚያውቁ በአዲሳባ ዊንጌት ሠፈር ያደጉ አንባቢ አርቲስቶች ከእነ ጠቢቡ ሠሎሞንና ከእነ አቤሰሎም፣ ነፍሱን ይማርና ከእነ ተስፍሽ ጋር አንዴ በፒያሳ በኪራይ በምንኖርበት ግቢ ስለ ልጅነታችን እያነሳን ስንጨዋወት - ይሄን ‹‹ቴሪዎሼችካ›› የተሰኘ የልጅነት መጽሐፍ ለካ ሁላችንም አንብበነዋል። እና በስተርጅናችን ላይ የልጅነት መዝሙራችንን በህብረት በዜማ ወጣነው:- «ልጄ ቴሪዎሼችካ፣ ና ብላ ምሳህን፣ ማሩን ከወተት ጋር፣ የሠራሁልህን...»። አቤት ደስታ! አቤት ሳቅ! እርግጠኛ ነኝ የሩሲያም ህጻናት ያደጉበት የተረት መዝሙር ነው። የህጻናት ተረቶች ድንበር ዘለል ሰብዕናን የሚሰጡ፣ ድንበር ሳይገድባቸው ለሁሉም ህጻን ደስታ የተሞላባትን ዓለም በምንባብ የሚያስጨብጡ ዕፁብ ገጸ በረከቶች ናቸው።

‹‹ጥንቸል ጴጥሮስ››። ‹‹ውርዬ››። ‹‹የእንስሳት ጉበዔ››። ‹‹አለቃ ገብረሃናና ተረቶቻቸው››። ‹‹ጦጢት››። ‹‹ምርጥ የግሪም ተረቶች››። ‹‹አንድ ሺህ አንድ ሌሊት›› (በእርግጥ አዋቂዎችም ቢያነቡት የሚፈነጥዙበት - ህጻናትን ግን እልም አድርጎ የሚያደስት ትርጉም መጽሐፍ)። ብዙ ናቸው ሁሉም ባንዴ ትዝ አይሉኝም። ሌላውን የእኔ ዘመን ልጆች የነበራችሁ ጨምሩበት። በአጠቃላይ ግን ዋናው ለመናገር የምፈልገው ነገር.. የንባብ ልምድና ፍቅር ከእነዚያ ትናንሽ የሕጻናት ገጾች የሚጀምር መሆኑን ነው። በስዕሎች የተሞሉ፣ ትናንሽ ለአዋቂ ‹‹ሴንስ›› የማይሰጡት እነዚያ መጻሕፍት ናቸው የልጆችን አዕምሮ ከፍተው ከንባቡ የምናብ ዓለም ጋር በጊዜ የሚያስተዋውቁት።

እና - ዛሬ ላይ ያላችሁ ወላጆች - አደራ ለህጻናት ልጆቻችሁ - ገና ከጮርቃነታቸው ጀምሮ - የተረት መጻሕፍትን ሳትንቁ ገዝታችሁ አስነብቧቸው። ዛሬ ላይ ለልጆቻችሁ የምታበረክቷቸው ትንንጥዬ መጻሕፍት - ልክ ችግኝን አፈር እንደማስታቀፍ፣ ውሃ እንደማጠጣት ማለት ናቸው። በኮተኮታችኋቸው አቅጣጫ ልጆቻችሁ በዚያው የንባብ ልምድና የምናብ ዓለም ታንጸው ያድጉላችኋል።

ከልጅነት የተረት መጻሐፍት ከፍ ስል በዕድሜ እኩዮቼ ጭምር የሚዘወተሩ አነስ ያሉ ልብወለዶችን ለማንበብ መንደፋደፍ ተጀመረ። ለመጀመሪያ ጊዜ አባቴ የሆነች ‹‹Unwilling Betrothal››የምትል የእርሱን ዘመን ቆየት ያለች የእንግሊዝኛ ፊክሽን የእነ ማርክስ «ዳስ ካፒታል» መጻህፍት ከሃርድ ከቨር ካርቱኖቻቸው ከተደረደሩበት ሼልፉ መዝዘ ሰጠኝ። ለወራት ከመዝገበ ቃላትና አቅራቢያዬ ከተገኙ ወጣቶች ጋር ቃላቷን እያመሳከርኩ ታገልኳት። እና ያቺ የእንግሊዝኛ ድርሰት የመጀመሪያውን የድርሰት ዓይኔን ከፈተችልኝ።

ቀጥሎ ‹‹ዶን ኪኾቴ›› የምትል ትርጉም የት/ቤት ጓደኛዬ ሲሳይ አበረከትልኝ። ታገልኩ ከዶን ኪኾቴም የእብደት ዙረቶች ጋር። ቀጥሎ ‹‹ጣምራ ጦር›› የምትል በሶማሊያ የዘመቱ ኢትዮጵያውያንን እውነተኛ ታሪክ የምትተርክ የእነ በሪሁንና አለባቸውን ድርሰት አነበብኩኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከድርሰቶች ሁሉ እጅግ መሰጠኝ። ከፍ ያለ የጀብዱና የሀገር ፍቅር ስሜት ያሳደረችብኝ አጓጊ መጽሐፍ - ት/ቤታችን የዕረፍት ሰዐትን እየጠበቅኩ ከረዥም ቀናት ትንቅንቅ በኋላ የጨረስኳት መጽሐፍ ነች። ከዚያ ሌሎች ልብወለድ መጻሕፍትን ከዘመኔ ወጣቶች ጋር ወደ መዋዋስና ወደ ማንበብ ተሸጋገርኩ።

እዚህ ላይ ስሟን ሳልጠቅሳት የማላልፋት ሐረር ቀበሌ 10 ሰፈር ውስጥ ‹‹ቅድስቴ›› የተባለች የጓደኛችን የሣሙዔል ታላቅ እህት ነበረች። ሃይስኩል ስገባ ጀምሮ ብዙ መጽሐፍትን አውሳኛለች። ወይም ተቀያይረናል። ይገርመኛል ከሰፈሯ ልጆች ሁሉ ተለይታ የነበራት የማንበብ ፍቅሯ። አሁንስ እንዴት ትሆን ይሆን? የት ነች? የማንበብ ልምዷስ? ልጆች ወልዳስ... ልጆቿንስ እያስነበበቻቸው ይሆን?... አላውቅም። አንድ ቀን ሳሚን መጠየቄ አይቀርም። ግን ውለታዋን ሳልረሳ ላመሰግናት እፈልጋለሁ።

‹‹ዶ/ር ኤሪካ ቬርነር››። ‹‹ብርቅርቅታ››። ‹‹አስኳል››። ‹‹ባይተዋር››። የቶማስ ሀርዲ ‹‹ወይ ፍቅር››። ‹‹እፎይታ››። ‹‹ዲቃላው››። ‹‹ማነው?››። ‹‹በቀለኞች››። ‹‹ምንዱባን›› (‹‹መከረኞች››)። ‹‹አዳኝና ታዳኝ››። ‹‹የተሸጠው ሸርጣን››። ‹‹ቃልኪዳን››። ‹‹የታንጉት ምስጢር››። ‹‹ወርቃማው ጓዳ››። ይሄን መጽሐፍ የዘመኔ ወጣቶች ብልግና ያለበት ድርሰት ስለሆነ ወላጆቻችንን እየተደበቅን ነበር እየተዋዋስን እናነበው የነበረው።

ይሄን መጽሐፍ ሳስብ «Body Chemistry» የሚለው የማይክል ዳግላስና የሻሮን ስቶን ፊልም ይመጣብኛል። የድብቅ ፈንጠዚያዎቻችን ነበሩ ሁለቱም። አንዱ በመጽሐፍ ሌላው በፊልም።

በተለምዶ «ጁንየር» እየተባለ በሚጠራው በሀረር ሲኒየር ሃይስኩል በዘበኝነት ይሰሩ የነበሩ አንድ ሽምገል ያሉ የቀድሞ ሠራዊት ሻምበል ማዕረግ የነበራቸው ሰው ነበሩ። ይገርሙኛል። ሁሌ በታችኛው በር በኩል ነበር ጥበቃ የሚመደቡት። ሁሌ መጻሕፍት ከእጃቸው አይለያቸውም። በሀረር ጁንየር ት/ቤት የተማሩ እኩዮቼ እንደሚያታውሷቸው አልጠራጠርም። «ሻምበል» ነበር የምንላቸው። ስማቸው ተዘንግቶኛል። «ፀጋዬ» ይመስለኛል። ረስቼዋለሁ። በወቅቱ እኚያ ታላቅ አባት ታላቅ ውለታን ውለውልኛል። በአጥር እየቀደድን ከት/ት እንፎርሽ የነበርነውን ወጣቶች - በሚገርም ፍቅርና ትዕግሥት - ወደ መጽሐፍ አንባቢነት ለመቀየር የቻሉ - ከመምህር የበለጡ የጥበብ መምህሬ ነበሩ። ብዙ መጻሕፍትን አውሰውኛል። «የተራራው ምርኮኞች»። «የመጨረሻዋ ቅጠል»። «ሾተላዩ ሰላይ »። «በረመዳን ዋዜማ»። «30 ደቂቃ በኢንቴቤ»። «ታላቁ ሴራ»። «ሞሳድ»። «ኬጂቢ»። «ስድስቱ ወንጀለኞች»።

እና ሌሎችንም ብዙ ድርሰቶችን አውሰውኛል እኚያ በወቅቱ እጅግ የማከብራቸው - አሁን ደግሞ ጊዜ ያለ ቦታቸው የጣላቸው ትልቅ መኮንን መሆናቸውን ወደ ኋላ አውጠንጥኜ የተገነዘብኩላቸው - እኚያ የትምህርት ቤታችን የጥበቃ ባልደረባ ሻምበል። የስንቱ ውለታ አለብኝ። መለስ ብዬ እነዚያን ሰዎች መጎብኘት አለመቻሌ ብዙ ጊዜ ያበሳጨኛል። ያስቆጨኛል። በወጣሁበት የቀረሁ የማልረባ የሕይወት ተጓዥ ነኝ እላለሁ። ለእኚያ ሰው በህይወት ካሉ የበዛ ግርማ ሞገስን እመኝላቸዋለሁ።

ከዚህ በፊት ስሙን በወጉ አንስቼ ያመሰገንኩት ጎረቤታችን ጋሼ ይልማ መሸሻ ደግሞ አለ። እርሱ ደግሞ ከውጪ ተወዳጅ ፖፑላር ድርሰቶች በተለይም ከእነ ኧርቪንግ ዋላስ፣ ሲድኒ ሼልደን፣ ዳኔላ ስቲል፣ ማሪዮ ፑዞ፣ ቶም ክላንሲ፣ ወዘተ ጋር ያስተዋወቀኝ የንባብ አርዓያዬ ነው። የሰፈሩን ወጣቶች ልቅም ያሉ ውብ የውጭ ድርሰት ትርጉሞችን ነበር የሚያስነብበን። በነፃ ውሰት። «በሬ ካራጁ»። «እሾህን በእሾህ»። «የፍርድ ቀን ዘመቻ» (አብይ አፈወርቅ የማትሪክ ፈተና ዋዜማ ላይ ድጋሚ ያዋሰኝና ጉድ የሰራኝ - ኋላ ተርጓሚውን በአካል አግኝቼ ብዙ የተጨዋወትኩት ዋናው «ዘ ዱምስዴይ ኮንስፓይረሲ» የሚል ልብ አንጠልጣይ ድርሰት!)፣ «ቃል»፣ «ወይ ፍቅር»፣«ውሸንፍር»፣ «የካይሮው ጆሮ ጠቢ»፣ «በሰላይ ላይ ሰላይ»፣ «የጡት አባት»፣ «የኦሽዊትዝ ምስጢር» (ይሄ እውነተኛ የናዚ ዶክተር ሜንጌሌ አሰቃቂ ታሪክ ነው)። «ጃኩሊን»። «ስም የለሽ»።

ሌሎችም በአፍላ ወጣትነት በፍቅር ያነበብኳቸውና የማይረሱኝ የሲሳይ ንጉሡ ደጋግሜ ያነበብኩት «ሰመመን»። «ማዕበል»። «ለምን አትሞትም?»። «ሀዲስ»። «ኦሮማይ»። «ደራሲው»። «ከአድማስ ባሻገር»። «ፓፒዮ»። «የልም እዣት»። «ፍቅር እስከ መቃብር»። «ሰባተኛው መልዓክ»። «አምስት ስድስት ሰባት»። የመስፍን ሀብተማርያም ወጎች «የቡና ቤት ስዕሎች...»። «አውዳመት» እና በአንድ ወቅት የዩኒቨርሲቲ ፍሬሽማን ተማሪ እያለሁ ከጓደኛዬ ብንያም ተዘራ ጋር ተወራርጄ ስዘረዝራቸው በቁጥር ከ120 በላይ የደረሱ ሌሎችም ብዙ የሀገር ውስጥና የውጭ ድርሰቶችን ኮምኩሜያለሁ በጊዜዬ።

ሃይስኩልን ጨርሼ ወደ 6 ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ካምፓስ ስገባ ገና 17ኛ ዓመት ልደቴን አክብሬ 18ኛዬ ላይ አልደረስኩም። ገና አፍላ ወጣት ነበርኩ። በዕድሜ። በንባብ ዕድሜዬ ደግሞ - ዕድሜ ለዘመን እኩዮቼ እና ቁጥራቸው ለበዛ የዘመኔ ባለውለታች - ሳላጋንን በንባብ ዕድሜዬ አንድ አንባቢ የ40 ዓመት ጎልማሳ ከሚያነባቸው መጻሕፍት ያልተናነሰ መጻህፍትን ያጣጣምኩ - ከፊል የምናብ ከፊል የእውኑ ዓለም ሰው ሆኜ ነበር። ብዙዎቹን የማውቃቸውን ነገሮች ያወቅኩት ከንባብ ህይወቴ ነው ማለት እችላለሁ። ከሳይኮሎጂና ፍልስፍና አስተሳሰቦች ጋር ካስተዋወቀኝ ከዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ ጀምሮ ደግሞ - ይዘታቸው ጠንከር ያሉ ክላሲካል ልብወለዶችንና ድርሰት ያልሆኑ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በምሁራን የተጻፉ ሲሪየስ ስታፎችን ወደማንበብ ተሸጋገርኩ።

እነሆ ከልጅነቴ የግችሌ ሜዳና ቴሪዎሼችካ ድርሰቶች - እስከ ዶስቶየቪስኪ ብራዘርስ ካራማዞቭና የኒኮላይ ጎጎል ዴድ ሶልስ ድረስ፣ ከልጅነቴ ምርጥ የግሪም ተረት መጽሐፍት እስከ ጉልምስናዬ ምርጥ የኖአም ቾምስኪ መጽሐፍት ድረስቼ፣ ከልጅነቴ የእንስሳት ጉባዔ እስከ እርጅና ዘመኔ የእንስሳት ዕድር ድረስቼ ይኸው ድሮም፣ አሁንም፣ አነባለሁ። መጽሐፍት ያዋዙኛል። ብቸኝነቴን ያስረሱኛል። በህይወት ልምድና በኑሮ አጠገባቸው ሊያስደርሱኝ ከማልችላቸው ታላላቅ የዓለማችን ሰዎች ጋር ያውሉኛል። ጽሑፎቻቸውን ቁጭ ብዬ እየታደምኩ፣ እየተመሰጥኩ፣ እየተጨቃጨቅኩ እወያያለሁ ከሞቱም በህይወት ካሉም ደራሲዎች ጋር። ከጥንታዊ ጸሐፍት እስከ ዘመናይ ጸሀፍት ዘመንና ዕድሜ ሳይገድበኝ - እመላለሳለሁ በዘመኖች መካከል። በሌላ በምንም ምክንያት ግን አይደለም። በማንበብ ልማዴ ብቻ።

ከልጅነት ከሰፈር ኳስ ጨዋታ እኩል በጀመርኩት የንባብ ልምዴ የተነሳ። በዚህች አጭር ሕይወቴቼ እትብቴ እና ልቤ ከተተከለባቸው እጹብ ድንቅ ሥፍራዎቼቼ በተለያዩ የህይወት ጥሪዎች አስገዳጅነት እየተፈናቀልኩቼ በብዙ አስቸጋሪ ሥፍራዎች ለመኖር ተገድጄያለሁ። ብዙ ርቀቶችን ተጉዤ፣ ብዙ ጠመዝማዛ መንገዶችን አልፌያለሁ። ለአንድም ቀን ግን ምንም ነገር እንግዳ ሆኖብኝ አያውቅም። ለአንድም ቀን ፍጹም ብቸኝነት ተሰምቶኝ አያውቅም። አንድም ከምናቦቼ ጓዳ አውጥቼ የምጽናናባቸው የምናብ ዓለም አኗኗሪዎች ስላሉኝ። ሁለትም መጽሐፍትን በየሄድኩበት እንደ ልብ ጓደኛ አጥብቄ ስለምይዝ፣ መጽሐፍት ስለማይለየኝቼ ፈጽሞ ብቻዬን ሆኜ አላውቅም። ፈጽሞ የማዋየው አጥቼ አላውቅም። ብቸኝነት የሚሉት ህመም ቢፀናወተኝም - በፍጹም ግን ፍጹም መለመላ ብቻዬን ሆኜ የተፈጠርኩ ያህል ብቸኝነት ተሰምቶኝ አያውቅም።

ወደ ገፅ 15 ይዞራል

አዲስ ሰፈር

ፈገግ የሚያሰኘው <ያራዳ ዘበኛ> አጀማመር እና <ሰባራ ባቡር> የሚለው የሰፈር ስያሜ አመጣጥ

እምነት ታደሰ ወልደጊዮርጊስ፣
ተባባሪ ፕሮፌሰር፣
ጆሃንስበርግ ዩንቨርሲቲ

ከአድዋ ድል በኋላ አጤ ምኒሊክ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ ከጀመሩት አዲስ ዘመናዊ ትልሞች አንዱ እቅዳቸው መኪና ማስመጣትም ስለ ነበር ፤ ለመኪና የሚመች መንገድ ዝግጅት ማድረግ አስፈለገ። ለዚህም ተግባር ያዲስ አበባ የመጀመሪያው የማዘጋጃ ቤት ሃላፊ አርመናዊውን ሳርኪስ ቴርዚያንን ዳምጠው እንዲያመጣ አዘዙት።

ይህንን ባቡር ነው ሕዝባችን በዘልማድ የተርኪስ ባቡር ብሎ የሚጠራው የነበረው። ዳምጠውም በእንፋሎት የሚሰራና ብዙ ድምጽና ጭስ እያወጣ የሚሄድ በመሆኑ ለሕዝባችን ትልቅ ትንግርት ሆነ። ባቡሩን ለማየት የአዲስ አበባ ሕዝብና ከሩቅ ድረስ ስንቅ ይዞ የመጣው የህዝብ ብዛት ባቡሩን በመክበብ አላንቀሳቅስ አለው። አንዳንዱም በመገፋፋትና ደንብሮ በመሮጥ የባቡር ጠለፋ መሆን ጀመረ።

ይህንን የባቡሩን ስራ እንዳይስተጎጉልና ሰውም እንዳይጎዳ ወጣት ተመልምሎና ሰልጥኖ የባቡሩ ዱላ ይዞ ስራ እንዳይስተጎጎል ከቦ የሚቆመው ሰራዊት ነው የመጀመሪያው ያራዳ ዘበኛ የተባለው። በኋለኛው በልጅ እያሱና ፤ በንግስት ዘውዲቱና በኋላም በተፈሪ ዘመን የገቡትን መኪናዎች ፊት ፊት እየሮጠና ሰውና ከብት የሚያባርረው ይሄው ያራዳ ዘበኛ በየመኪናው እየተመደበ ነበር።

የተርኪስ ባቡር ብዙ ያዲስ አበባ መንገዶችንና ያዲስ አለምና ሌሎችን መንገዶች ካደላደለ በኋላ ብዙ ጊዜ እየተበላሸ ከውጭ አገር መለዋወጫ እየመጣለት ካገለገለ በኋላ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ መጨረሻ ተበላሽቶ በቆመበት ቀረ። ሰፈሩም ሰባራ ባቡር ተባለ።

በምስሉ የምታዩት አጤ ምኒሊክ ዳምጠው ካስመጡ ቡኃላ ስራውን በመመልከት ላይ እንዳሉ ነው።

መልካም የትንሳኤ በዓል

RANK
Specialized Dermatology Clinic

No . 1 0943 505050
Wollo Sefer, tk building 3rd floor

No . 2 0943 0947 515151
Lebu, sabeh building 3rd floor
in front of gara mart

ከገፅ 13 የዞረ

ዕድሜ ለመጻሕፍት ወዳጆቼአ ዕድሜ ለማይታክቱና እገሌ እጅ ልግባ አልግባ ብለው ለማይመርጡት ደራሲያን! ዕድሜ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ባለፍኩበት የህይወቴ መንገዶች ሁሉ የንባብን ፍቅር በውስጤ ለተከሉ ውድ እና ድንቅ ኢትዮጵያውያን ባለውለታ ወገኖቼ! ዕድሜ ለአርአያዎቼ፣ ለዘመን ታላላቆቼ፣ ለዕድሜ እኩዮቼአ አንድዬ ዕድሜን በዕድሜ ላይ ይጨምርላችሁ! ከህይወት መዝገብ ስማቸውን አኑረው በአካል ላለፉት የመጽሐፍት ወላጆቼና ባለውለታዎቼ ደግሞቼ ፈጣሪ አምላክ የበዛ ገነተ ሠላሙን ይሰጣችሁ፣ ያሳርፋችሁ ዘንድ የልብ ምኞቴ ነው!

ዛሬ ልጆች ወልዳችሁ ለመሳም ለበቃችሁ አንድ የማስተላልፈው መልዕክት አለኝ፡- አደራ ለልጆቻችሁ በጊዜ ገና በጊዜ ከወተት ጋር መጽሐፍትን አላምዷቸውአ ይጥቀምም አይጥቀምም - ካለማንበብ ማንበብ ይሻላልና። ልጆቻችሁ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ መቼም ብቻቸውን አይሆኑምና። የ3ሺህ ዘመን የጽሑፍ ታሪክ ያላት የኢትዮጵያ ልጆች ነንአ አንባቢ አባቶች ነበሩንአ አንባቢ ትውልድ መፍጠር ደግሞ የኛ ፋንታ ነው!

በአንባቢ ትውልድ የበለጸገች መልካም ኢትዮጵያን ከልብ ተመኘሁ!



ተስፋዬ ገብረአብ ስለ ስብሃት ገብረ እግዚአብሄር

ለጋሽ ስብሐት ገብረ እግዚአብሄር ለስድስት ዓመታት ያህል አለቃው ሆኜ ብንሰራም በአንዳንድ ነገሮች ላይ እርሱ ነበር የሚያዘኝ። አንድ ቀን እንዲህ ሲል ጠይቆኛል።

“ላማክርህ ነበር የመጣሁት”
“እሺ ጋሽ ስብሐት ምን ነበር?”
“ገንዘብ ቸግሮኛል”

ዝም አልኩ። ምክንያቱም የመጨዎቹን ሁለት ወራት ደመወዙን ከወዲሁ ወስዶ ነበርና ምን እንደማደርግ ግራ ሊገባኝ ጀምሮ ነበር። እሱም ይህንን ተገንዝቦ ኖሮ ፈጥኖ ንግግሩን ቀጠለ።

“ደመወዜን ቀድመህ ስጠኝ ልልህ አልችልም። ወስጄዋለሁና። አሁን ሳስብበት ቆየሁና አንድ ሌላ ዘዴ መጣልኝ።
“ምን ዘዴ አገኘህ ጋሽ ስብሐት?”

“ታታሪ ሰራተኛ በሚል ለምን ቦነስ አትሰጠኝም?”

እንኪን ለትንሳኤ በዓል አደረሳችሁ

©Bored Cellphone Addis Ababa

ሀገርኛ ታሪክ

ልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ አባታቸው ዳግማዊ ቴዎድሮስ በመቅደላ ጦርነት በጀግንነት ተዋግተው ራሳቸውን ከመሰዋታቸው በፊት፣ 'ልጄን አለማየሁ አደራ' ብለው በመቅደላ እስር ቤት ላሉ ሚሲዮናውያን በሰጡት የአደራ ቃል መሰረት፣ ሚስዮናዊያኑ ወደ እንግሊዝ ወስደውት በልዑል መዓረግ ኖሮ በልጅነቱ ነቀረ የተቀጨው።

ንግስት ቪክቶሪያ በቀን ማስታወሻዋ (Diary) ላይ ስለ ልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ ህልፈት አስመልክቶ የተሰማትን ሀዘን እንዲህ ገልፃዋለች፦

"በአይኑ ቀለም ምክንያት ሰዎች ለየት አድርገው እንደሚመለከቱት የሚገነዘብ፣ ሀሴት የራቃት ህይወት የኖረ፣ ይሄንን የመሰለ መልከ መልካምና ቅን ልዑል ከቤተሰቦቹ ርቆ ኖሮ ሳይገናኛቸው ማለፉ እጅግ ልብ ይሰብራል"...

Queen Victoria mentioned the death of the young prince in her diary, saying:

"What a good, kind and such unhappy Prince he had been and how sad it was that he should die so far from his family."

ልዑል አለማየሁ ከአባቱ ህልፈት በኋላ ከሁለት ያጣ [እዚህ ቢቀር ካሳ ምርጫ (አፄ ዮሀንስ አራተኛ) የንጉስ ልጅ ስለሆነ እንደ አባቱ በስጋት ሊገድለው የሚችል፤ እንግሊዝ ሄዶ እንዳይኖር የብቸኝነት ድባቴ የጎዳው] ልዑል ሆኖ በመኖሩ፣ በመቃብሩ ስር የሚከተለው ማስታወሻ እንዲፃፍለት በጠየቀው መሰረት ተጽፎለታል።

"እነሱ አመጡኝ፣ እኔ ግን ባይተዋር ሆኜ ኖርኩ።" (ልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ)

"I was a stranger and ye took me in" - (HIH Prince Alemayehu Tewodros)

የመፅሃፍት ጥቆማ

(እላፊ - መንገደኛ ፪)

በወሰንአየሁ - ሃያሲ

‘አንዳንድ ሰዎች ካለ ቦታቸው ይገኛሉ፤ ይህንን ሲያውቁ ወደ ቦታቸው ለመመለስ የሚተጉ ጥቂቶች ናቸው፤ ወደ ቦታቸው መመለስ የማይሆንላቸው አሉና:: ጥቂቶች ግን በዚህም በዚያም ብለው ይመለሳሉ::

ለዚያውም ባለ ሁለት ሰይፍ ተዋጊ ሆነው፣ ተዋጊ ብቻ ሳይሆን ድል አድራጊ ሆነው ይከሰታሉ:: ይህንን ማድረግ ከቻሉ ጥቂት ሰዎች መሃል መመደብ የሚቻል ይመስለኛል ፡- ዮርዳኖስ አልማዝ ሰይፉን

ምክንያቱም ዮርዳኖስ ተመራማሪ ነው:: የነፍስ ጥሪው ግን ፀሐፊነት እና ደራሲነት ነው :: ለዚህም አባባሌ ምሳሌ የሚሆነኝ "እላፊ - መንገደኛ፪" የተባለ መፅሐፉ ነው::

እንዳልኳችሁ ዮርዳኖስ፣የማህበራዊ ሳይንስ ባለሞያ እና ተመራማሪ ነው:: ከኢትዮጵያ እስከ ደቡብ አፍሪካ ባለው የስደት መስመር የስደተኛውን የስደት ሕይወት ይመረምራል፤ ይፈትሻል ወዘተ:: እናም በማሕበራዊ ባለሙያነቱ የቃኘውን የኢትዮጵያውያን ስደተኞች ሕይወት መልሶ ያስቃኘናል::

የስደተኛውን ሕይወት የሚያስቃኘን ደረቁን ጥናታዊ ፅሁፍ ሰልቆ፣ በስነፅሁፋዊ ተውህቦ አጣፍጦ፣ በስነ ቃል አስጊጦ፣ በግጥምና በዘፈን (በዜማ) እየዋዛወዘተ ነው:: በሌላ አነጋገር ስደት "ቀፋፊ ነው" ብሎ አያደርቅህም:: ቀፋፊነቱን በሰዎቹ (በገፀ ባሕርያቱ) የእለት እለት ሕይወት ውስጥ ያሳይሃል:: ሲከፋቸው መከፋታቸውን፣ ሲስቁ ሳቃቸውን፣ ሲደንሱ ዳንሳቸውን ወዘተ እያስቃኘ በተለያየ ስሜት ውስጥ ይዘፍቅሃል:: ለዚህ ደግሞ የረዳው ስነ ፅሁፋዊ ክህሎቱ ነው፤ ለዚህ ነው ከላይ መንደርደሪያዬ "አንዳንድ ሰው ካለ ቦታቸው ይገኛሉ ፤ ይህንን ሲያውቁ ወደ ቦታቸው ለመመለስ የሚተጉ ግን ጥቂቶች ናቸው" ያልኩት:: ዮርዳኖስ ደረቅ ጥናትን እንዴት ተነባቢ አድርጎ ማቅረብ እንደሚቻል በማሳየት ረገድ የተዋጣለት ሆኖ ስላገኘሁትም ነው::

"እላፊ መንገደኛ ፪" በ505 ገፅ የተጠረዘ ደጎስ ያለ መፅሐፍ ነው:: እንዲያም ይሁን እንጂ የፈለግከው ገፅ ላይ፣ የፈለግከውን ርዕስ መርጠህ ማንበብ ትችላለህ:: እያንዳንዱ ርዕስ በታሪክም ይዘት ሆነ በአተራረክ ዘይቤ የተሟላ ሆኖ የቀረበ ነው::

በአጭሩ ዮርዳኖስ ደረቁን የማሕበራዊ ሳይንስ ጥናት አይነግርህም:: በሰላ ብዕር አዋዝቶ፣ በጥበብ ከሸኖ ነው የተባ ዕውቀት የሚያሸርህ:: ይህም ብቻ አይደለም፤ ለሌሎች ምሁራኖቻችንም ትልቅ መልዕክት ያስተላለፈ መፅሐፍ ይመስለኛል:: ጥናቶች በምሁራን አምባ ታሽገው ከሚቀሩ በዚህ መልኩ ማሕበረሰቡ ጋ ማውረድ (ማድረስ) ይቻላል የሚል::

የሆነ ሆኖ መፅሐፉን አንብቤ ስጨርስ "ዮርዳኖስ፣ ከማሕበራዊ ሳይንስ ባለሙያነት ይልቅ ደራሲነት ነበር መክሊቱ" አሰኝቶኛል:: ድንቅ መፅሐፍ ነው!!! ዋጋው ደግሞ ኪስ አይጎዳም፤ የአንድ ምሳ ዋጋ በሉት:- 250 ብር!

ዮርዳኖስ አልማዝ ሰይፉ ከኢትዮጵያ ደቡብ አፍሪቃ ድረስ በተዘረጋው የስደት ሰንሰለት ውስጥ የሚከናወኑ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኹነቶችን የሚያጠና የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ነው:: የምርምር ሥራዎቹ የሚያተኩሩት የኢትዮጵያውያን ስደተኞች ድህነት እና የኑሮ ደረጃ ልዩነት (poverty and inequality) ከስደት ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ነው:: በእነዚሁ ጉዳዮች ላይ ባለፉት ሰባት ዓመታት ያሳተማቸውን የጥናት ወረቀቶች ወደ መጻሕፍት የቀየረ ሲሆን ከዞህ ቀደም “መንገደኛ” በሚል ርዕስ ያሳተመው መጽሐፉ “Wayfarers” በሚል ርዕስ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሟል::

“እላፊ፤ መንገደኛ ፪” በክብሩ መጻሕፍት መደብር(ትራኮን ታወር)፣ ጃዕፈር መጻሕፍት መደብር (ለገሃር) እና በሌሎችም መጻሕፍት መደብሮች ይገኛል:: የገጹ ብዛት 505 ሲሆን ዋጋውም 250 ብር ነው::

ከርቱዕ አንደበት

<ልጄ ሆይ አነጋገርህን ጠብቅ፥ ራስህን ዝቅ ዝቅ አድርግ፥ አረማመድህ በዝግታ ይሁን። ማየትህ ወደ ታች እንጂ ወደ ላይ አይሁን።>
ጠቢቡ ሰሎሞን

<የዓለም ፍቅሯና ጣዕሟ እንዳያስትህ ተጠንቀቅ። እርሷ ካንተ በፊት ለነበሩት አልነበረችላቸውም፤ ዛሬም ላንተ አትኖርልህም፥ እንዳንተ ላሉትም አትኖርላቸውምና።>
ሶቅራጥስ

<አስተውል.....የዕብደትን ምሬት ያልቀመሰ ሰው የዕውቀትን ጣዕም አያውቅም። ዳግመኛም ሥጋዊ ፈቃድን መፈፀም አንተን የዘመን ተገዥ ታደርግሃለች። ሥጋዊ ፈቃድን አለመፈፀም ግን፥ ዘመንን ያንተ ተገዥ ታደርገዋለች።>
አፍላጦን

<ከህዋሳቶችህ አንዷ ብትታመም መላ ሕዋሳቶችህን ሁሉ ጨምራ እንዳታጠፋ ፈርተህ እንደምትቆርጣት ሁሉ፥ እንደዚህም ክፉ ምኞት ነፍስህን ድል ባደረጋት ጊዜ የተመኘችውን በመንሳት ልትቆጣጠራት ይገባል፤ መሻትና ምኞት የልብ ጠላቶች ናቸውና!>
ሶቅራጥስ

ጋሊኖስ እንዲህ አለ፥ <ጠባዩን ያፀናና ከሁሉ ጋር የተስማማ ሰው፤ ምክሩ የቀና፣ ፍቅሩ የጸና ይሆናል። ተወዳጅነቱም በብረት ላይ እንደተቀረፀ ምስል በሚወዱት ሰዎች ልብ ተቀርፆ ይኖራል።>

<ቁጣ የሚያሸንፍህ የሆነ እንደሆነ ቅን ሐሳብህን ለውጦ የራሱ ተከታይና ተገዢ ትሆን ዘንድ ማርኮሃልና ራስህን ከሰው ወገን አትቁጠረው።>
ሶቅራጥስ

<ነፍስ ስጋን ካላሸነፈቻት፥ እንግዲህ ሥጋ ለነፍስ መቃብር ሆነች ማለት ነው።>
ፒታጎሮስ

<የነፍስ ክብሯ መከራን፣ ተድላን እና ደስታን አንድነት አድርጋ ትክክል በሆነ አቀባበል ስትቀበል ነው። ነፍስ የስጋ ምሰሶ ናትና። ነገር ግን የስጋን ሞት፥ ሞት እንደሆነ አታስብ። ሞትስ ማለት የነፍስ ሞት ናት።>
ሶቅራጥስ

ከፈላስፎች አንዱ እንዲህ አለ፥ <ለታማኝ ሰው አእምሮ ወዳጁ ነው። ትዕግስት እንደራሴው፥ ልቡና መሪው፥ በጎ ምግባር ግዛቱ፥ ፍቅር ወላጅ አባቱ፥ እውነት ዋጋው፥ ትህትና የሠራዊቱ አለቃ ነው።>

<በዚህ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ አኗኗራቸው የመንገደኛ አኗኗር መሆኑን ማወቅ ይገባቸዋል። መንገደኛው ከገባበት አገር አድሮ ሲነጋ ተነስቶ እንደሚሄድ ሁሉ እነርሱም ከዚህች ዓለም በሞት ተለይተው መሄዳቸውን መርሳት የለባቸውምና።>
አሪስጣጣሊስ

(ምንጭ - አንጋረ ፈላስፋ)

©Bored Cellphone Addis Ababa

(. . . ኮሮና የያዘኝ ለታ)

ደቻሳ አንጌቻ፣ የኮረማሽ የጉዞ ማህበር ሊቀመንበር

ባለፉት 15 ቀናት ኮቪድ አሞኝ እራሴን አግልዬ (ኳራንታይን አድርጌ) በማስታመም ላይ ነበርኩ። የምህረት አምላክ ለሆነው ፈጣሪ ምስጋና ይግባና አሁን ሙሉ ጤነነትና ብርታት ይሰማኛል። ናሙና ሰጥቼ የመጨረሻ ውጤቴን ኔጋቲቭ በመሆኑ ወደ ናፈቀኝ ስራዬ ተመልሻለው።

በቫይረሱ መጠቃቴን የጠረጠርኩበት አጋጣሚ እንዲህ ነበር። ከስራ ወጥቼ ምሳ ወደማወዘወትርበት ቤት ሄጄ ምሳዬን አዝዤ በምጠባበቅበት ቅፅበት ነበር የተለየ የህመም ስሜት እና ምልክቶቹን ማለትም ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ የማለት ስሜት፣ የመቅመሥና የማሽተት ስሜት ማጣት፣ መድከም፣ በላብ መጠመቅ፣...ያጋጠሙኝ። ይህ የተለየ የህመም ስሜት እንደተሠማኝ ምሳውን አቋርጬ ራይድ ጠርቼ ወደ ቤቴ ገባሁና እራሴን ወደ ማግለል ሄድኩት። በነጋታው ናሙና ሰጥቼ በኮቪድ-19 መያዜን አረጋገጥኩ።

በመቀጠል ለፆም ቅበላ አግኝቼው ምሳ አብሬው የበላሁትን ተጓዳኝ የጤና ችግር ያለበትን በእድሜ የገፋውን አባቴን በስልክ ደውዬ የጤናው ሁኔታ ጠየኩት። ጤናው ሙሉ መሆኑን ሲነግረኝ ትልቅ ሸክም ከላዬ ላይ ቀለልኝ። ምክንያቱን ከኔ መታመም በላይ ያስጨነቀኝ የአዛውንቱ አባቴ በኔ ምክንያት በቫይረሡ ተጠቅቶ ይሆን ወይ የሚለው ጭንቀት ነበርና ነው። ሌሎች በስራና በማህበራዊ ህይወት የተገናኘኋቸውን ሰዎችም ኮቪድ ፖዘቲቭ መሆኔን ነግሬ የጤናቸው ሁኔታ እንዲያዳምጡና ህመም ከተሠማቸው ምርመራ እንዲያከናውኑ አሳሰብኳቸው።

የመጀመሪያ 3-4 ቀናት የህመሙ ስሜት በንፅፅር ቀለል ያለ ነበር። የምግብ ፍላጎት ከማጣት፣ ከመጠነኛ ትኩሳት፣ ... ከመሠሉ በንፅፅር ቀለል ያሉ ህመሞች በቀር ከባድ አልነበረም። በኮቪድ ምክንያት የሚመጣው የምግብ ፍላጎት ማጣት ስሜት ግን በሌሎች ህመሞች ከሚፈጠረው የምግብ ፍላጎት ማጣት ፍፁም የተለየ ነበር። ቁርስ ላይ በፍቅር የምወደው ጨጨብሳ ለአይን ማየት አስጠላኝ። ምሳና እራት ላይ የማዘወትረው የስጋ ወጥ ምግቦች እሬት እሬት ይሉኝ ነበር። የመቅመሥ ችሎታ ማጣቴ የፈጠረው ስሜትም ጣፋጩን ማር ሳይቀር ስቀምስ ውሃ ውሃ ይለኝ ነበር።

ቀጣዮቹ ቀናት የነበረው የህመሙ ስሜት ግን ከመግለፅ አቅም በላይ በጣም ከባድ ነበር።



የጉሮሮ እና የአፍንጫ መድረቅና መፋቅ፣ ተከታታይነት ያለው እንደ ወተት የሚንጥ ብን ብን የሚል ደረቅ ሳል፣ የምግብ ፍላጎት ጨርሶ ማጣት፣ ኃይለኛ ትኩሳትና ራስ ምታት፣ አልፎ አልፎ ተቅማጥና ትውከት፣ ደረት አከባቢ የመታፈንና የመጨነቅ፣ መጠኑን ለመግለፅ የሚከብድ የወገብና የመገጣጠሚ አካላት ህመም ነበረው። ሌላ ነገር ሳይጨመር የምግብ ፍላጎት ማጣቱ ብቻው በሽታውን ለመቋቋም የሚደረገውን ግብግብ አስቸጋሪ አድርጎብኝ ነበር። ብቻ በአጠቃላይ ስሜቱ እጅግ በጣም ከባድ ነበር።

በእያንዷንዷ ቀጣይ ሰአት ሊመጣ የሚችል የበሽታው አዲስ የህመም ምልክት ያስጨንቃል። ከአሁን አሁን የመተንፈስ ችግር ገጥሞኝ እሞት ይሆን ወይ የሚል ፍራቻ የወለደው ጥርጣሬ ደጋግሞ አእምሮ ላይ ያቃጭላል። ይህ በትንፋሽ ማጠር እሞት ይሆን ወይ የሚለው የፍራቻ ስሜት፤ ከቤተሰብ ወዳጅ ጓደኛ ተለይቶ ለቀናት ለብቻ የሚደረገው አስጨናቂው የውሸባ ህይወት፤ እናም ሌሎች ስሜቶች ተደራርበው የሚፈጥሩት ስነ-ልቦናዊ ጫና በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

እናም ሀተታዬን ሳጠቃልል የኮቪድ-19 ስርጭት ከምንገምተው በላይ ተስፋፍቷል። ጉዳቱም ቀስ እያለ የእያንዳንዳችን ቤት እያንኳኳ ነው። በየመንደሩ ድንኳኖች እየተተከሉ ነው። በየቤቱ ሀዘን እየገባ ነው። በሽታው የገባ ሰሞን ወጣት አይገልም ይባል የነበረው ነገር ልክ አለመሆኑን እያየን ነው። ቫይረሱ በሁሉም የእድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን እያጠቃና እየገደለ ነው። ጤና ሚኒስትርና የህብረተሰብ ጤና ተቋም እንደ ሀገር ያሉን የመተንፈሻ መርጃ መሣሪያዎች /ቬንቲሌተር በሙሉ በኮቪድ ታማሚዎች ተይዘው ማለቃቸውን በየስልካችን መልእክት እየላከልን ነው።

እናም ከባድ የህመም ስቃይ አለፍ ሲልም ለሞት ሊዳርገን ከሚችለው ኮቪድ-19 ብቸኛው የመዳኛ መንገድ ከቫይረሱ ከመጠቃት በፊት መጠንቀቅ ነውና ለራሷችን አብዝተን እንጠንቀቅ። በኛ ምክንያት ሊጎዱ የሚችሉ በእድሜ የገፉና እንደ ስኳር፣ የደም ግፊት፣ አስም፣ የመሳሰሉ ተጓዳኝ ህመሞች ያለባቸውን ውዶቻችንን እናድን።

አፍና አፍንጫችን በአግባብ እንሸፈን!
አካላዊ ርቀታችን እንጠብቅ!
እጃችንን በሚገባ እንታጠብ!
ከአላስፈላጊ መሠባሠቦች እራሳችንን እናርቅ!

''አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን!''

Misrak Ber Dukem

ምስራቅ በር
ዱከም ሥጋ ቤትና ባር

ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ Since 1990

Misrak Ber Dukem Butcher & Bar

እንኳን ለትንሳኤ በዓል አደረሳችሁ



ቁ . 1፡- ዱከም

ቁ . 2፡- መስቀል ፍላወር ከናዝራ ሆቴል ፊት ለፊት

ትንሳኤ ኢትዮጵያ

መልካም የትንሳኤ በዓ

ሚያዝያ 24/ 2013 ዓ.ም

ደመራ DEMERA Media and Communication

ንዋይ ደበበ

ዳዊት ፍሬው ሀይሉ

ታሪኩ ጋንኪሲ
(ድሻታግና)

ቤቲ ጂ

ኤልያስ ተባባል
እና ሌሎችም...

ደመራ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን እንኳን
ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ እያለ
በዓሉን በማስመልከት በዕለተ ትንሳኤ ልዩ
የመዝናኛ ዝግጅት በፋና ቴሌቪዥን ከቀኑ
7 እስከ 9 ሰዓት ይዞላችሁ ይቀርባል።

Graphics Design and Print
Alula Yohannes Advertising
0911 871767